# በከተሞች ልማት የዳያስፖራ ተሳትፎ የተሞክሮ ሰነድ

# Diaspora Engagement in Urban Development Good Practice Document

የካቲት 2014 ዓ/ም

አዲስ አበባ

ክፍልአንድ፡- የጎንደር ከተማ አስተዳደር በልማት ስራዎች የዲያስፖራ አካላት ተሳትፎ መልካም ተሞክሮ ሠነድ (DIASPORA ENGAGEMENT IN DEVELOPMENT ENDEAVORS OF GONDAR CITY) .......... 3

ምዕራፍአንድ .......... 4

1.1. መግቢያ .......... 4

1.2. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/ .......... 4

1.3. የተሞክሮው ዓላማዎች .......... 5

1.4. ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት .......... 6

1.5. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ .......... 6

1.6. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ የትኩረት መስኮች (ወሰን) .......... 7

1.7. የከተማው ነባራዊ ሁኔታ .......... 7

1.8. በከተማዋ የዲያስፖራ አካላትን በተለያዩ የልማት ስራዎች ለማሳተፍ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች (Opportunities) እና ፈታኝ ሁኔታዎች (Challenges) .......... 10

ምዕራፍ ሁለት፡- የዝግጅትምዕራፍ .......... 11

2.1. የዲያስፖራ አካላትን በተለያዩ የልማት ስራዎች የማሳተፉ ዓላማ .......... 11

2.2. የዲያስፖራ አካላትን በዘላቂ የልማት ስራዎች ለማሳተፍ ካለ ዝግጅት አንፃር .......... 12

ምዕራፍ ሶስት፡- የትግበራ ምዕራፍ .......... 19

3.1. የአፈፃፀም ስርዓትና አደረጃጀት .......... 19

3.2. የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት .......... 20

3.3. ተሞክሮው ያመጣው ተፅዕኖ ወይም ፋይዳ .......... 20

3.4. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች .......... 22

3.5. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች .......... 23

3.6. የተገኙ ውጤቶች /ተሞክሮዎች .......... 23

ምዕራፍ አራት .......... 23

4.1. ዲያስፖራ አካላትን በልማት ስራዎች የማሳተፍ ስራው ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ ....................................................23

4.2. በቀጣይ በተለያዩ እርከን ባሉ የመንግስት አካላት ሊደረጉ የሚገባ ጉዳዮች...............................................................25

ክፍልሁለት፡-በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ልማት ስራዎች የዲያስፖራ አካላት ተሳትፎ ተሞክሮ ሠነድ (DIASPORA ENGAGEMENT IN DEVELOPMENT ENDEAVORS OF ADDIS ABABA CITY)...................... 27

ምዕራፍ አንድ፡- አስፈላጊነትና መነሻ ሁኔታዎች.............................................................................................. 28

ምዕራፍሁለት፡- የዝግጅትምዕራፍ............................................................................................................. 35

ምዕራፍ ሶስት፡- የትግበራምዕራፍ ............................................................................................................. 42

ምዕራፍ አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ ......................................................................................................... 44

ክፍልሶስት፡- CITY DIPLOMACY AND CITY NETWORKING; IMPLICATIONS TO ETHIOPIA'S CITIES... 47

REFERENCES ......................................................................................................................................... 60

## ክፍልአንድ፡- የጎንደር ከተማ አስተዳደር በልማት ስራዎች የዲያስፖራ አካላት ተሳትፎ መልካም ተሞክሮ ሠነድ (Diaspora Engagement in Development Endeavors of Gondar City)

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1. መግቢያ

የአገራችን ከተሞች በፕላን እየተመሩ በአግባቡ እንዲለሙ ካልተደረገ በከተሞች የሚስተዋለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ማስወገድ ካለመቻሉም በላይ በከተሞች የሚኖሩ ዜጎችን መሰረታዊ ፍላጎት ማቃለል ብሎም ከድህነት ማውጣት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ከተሞችን የማልማትና የማዘመን እንዲሁም ለኑሮና ለስራ የተመቹ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ እጅግ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል ከተሞችን ለማልማት የሚያስፈልገውን የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሃብት ለማግኘት የሚጠይቀውን ግዙፍ መዋዕለ ንዋይ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ማግኘት የማይቻል ከመሆኑም በተጨማሪ የከተሞች የልማት ስራ በመንግስት አቅም ብቻ ሊከናወን የማይችል መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

በመሆኑም በከተሞች ልማት ተጨባጭ የሆነ እድገት እንዲመጣ ካስፈለገ ከየከተሞች መንግስታዊ አስተዳደርና ተያይዞም ከሚመደብ የከተማ ልማት በጀት በተጨማሪ የአጋር አካላት የበጀት፣ የቁሳቁስና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡ በተለይም የዲያስፖራው ማህበረሰብ በሚኖርበት አገር ያፈራውን ሀብት፣ የቀሰመውን እውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ይዞ በመምጣት በአገሩ ቀጥተኛ ልማት በመሳተፍና የከተሞችን እድገት በማፋጠን በኩል የሚኖረው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያን ብሎም የጎንደርን ዲያስፖራ በከተማ ልማት ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ የሚያስችል የፖሊሲ እንዲሁም የፐብሊክ ዲፕሎማሲን ማበልፀጊያ እርምጃዎችን መውሰድ በአገር ውስጥም በከተሞች የአሰራርና የአደረጃጀት ማዕቀፎችን ማዘመን እና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ መዘንጋት የለበትም፡፡

## 1.2. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/

የተለያዩ የፅሁፍ ማስረጃዎች እንዲሁም መዋዕለ ዜናዎች በግልፅ እንደሚያሳዩት በርካታ አገሮች በዲያስፖራ ማህበረሰባቸው በሚደረግ ተሳትፎ በየአገሮቻቸው ከተሞች ጉልህ የልማት ስራዎች መከናወናቸው ብሎም አበረታች የኢኮኖሚ እድገት መመዝገባቸው በስፋት ይነገራል፡፡ (ለምሳሌ ቻይና፣ ህንድ፣ ፊሊፒንስ፣ ግብፅ፣ ናይጀሪያ ወዘተ) ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ዓለም ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ቁጥር በጣም ብዙ መሆኑ ይነገራል። ከዚህም ውስጥ ከ60% ያላነሰው ከጎንደርና አካባቢው የሄደ እንደሆነ ግምቶች ያሳያሉ። ሆኖም ባለው ዲያስፖራ ማህበረሰብ ልክ በከተማ ልማት ስራዎች ላይ ያለው ተሳትፎ አናሳ ነው።

ለዚህ ደግሞ ቀደም ብሎ ይስተዋሉ የነበሩ ችግሮች አሉ። እነሱም፡-

- ከፖለቲካ አመለካከት ጋር የሚያያዙ ችግሮች፤
- ከዘረኝነትና ጎጠኝነት ጋር የሚያያዙ ችግሮች፤
- ከማስተናገድ አቅም ማነስ፣ የመልካም አስተዳደር አለመኖር፣ ከአድሎአዊና ብልሹ አሰራር ወዘተ ጋር የሚያያዙ ችግሮች፤
- ከመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ችግሮች፤
- ከህዝብ ግንኙነት ስራዎች ደካማነት ወዘተ ጋር የተያያዙ ችግሮች።

## 1.3. የተሞክሮው ዓላማዎች

### 1.3.1. ጥቅል ዓላማ /General Objective/

የዲያስፖራው ማህበረሰብ በከተማው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ በበቂ ደረጃ ቀጥተኛና ጉልህ ተሳትፎ እንዲያደረግ ማስቻል።

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች /Specific Objectives/

**የዲያስፖራው ማህበረሰብ፡-**

- በግብርና እና ኢንዱስትሪ ልማት በተለይም በመድሃኒት ማምረት፣ የእርሻ መሳሪያዎችን እና ኬሚካሎችን በማምረት ላይ በበቂ ደረጃ እንዲሳተፍ ማስቻል፣
- በትምህርትና ጤና ልማት ተግባራት ላይ እንዲሳተፍ ማስቻል፣
- በሪልስቴት፣ በገበያ ማዕከላትና በድብልቅ አገልግሎት ሰጭ ግንባታዎች ልማት ላይ እንዲሳተፍ ማስቻል፣
- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በመሳተፍ የጎንደር ከተማን ታሪክ፣ ባህልና ቅርስ በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ የከተማዋን የቱሪዝም ልማት እንዲያሳድግ ማድረግ፣

- በሚኖርባቸው አገሮችና ከተሞች ከሚገኙ የሌሎች አገር ዜጎች ጋር በመግባባትና በመተማመን የልማት አጋርነትን /Development Partnership/ እንዲስፋፋ ማበረታታት፤
- በዘላቂ የከተማ ልማት ነክ ተግባራት የጥናትና ምርምር፣ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር ስራዎች ላይ የበኩሉን እንዲያበረክት ማስቻል።

## 1.4. ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት

- የጎንደር ከተማና አካባቢው ተወላጅ ሆኖ በተለያዩ የዓለም አገራት የሚገኘው ዲያስፖራ ቁጥር እጅግ በጣም ብዙ ስለሆነ በተሞክሮው መነሻነት በጎንደር ከተማ ልማት በተለይ በአገር ልማት በአጠቃላይ የሚኖረውን ተሳትፎ ለማስፋትና ለማጠናከር፤
- አሁን ያለውን ውስን ተሳትፎ ማሳደግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፤
- በዲያስፖራው አመቻችነት የጎንደር ከተማን የውጭ ግንኙነት ለማስፋትና ለማጠናከር ብሎም የኢንቨስትመንትና የቱሪዝም ፍሰቱን ለማሳደግ፤
- በዲያስፖራው ማህበረሰብ አካባቢ መነሳሳትን እና ቁጭትን በመፍጠር በሁለንተናዊ የከተማ ልማት ስራ ላይ ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል፤

## 1.5. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ

- በመጀመሪያ ከዲያስፖራ ግንኙነትና መስተንግዶ ስራዎች ጋር ቀጥታ ቀረቤታ ካላቸው የስራ ክፍሎች ውስጥ ማለትም፡- ከኢንቨስትመንት መምሪያ፣ ከቱሪዝም መምሪያ እንዲሁም ከከንቲባ ጽ/ቤቱ የትበልፅግ ጎንደር የፕሮጀክት ዩኒት ከፍተኛ ባለሙያዎችን በመምረጥ 3 አባላት ያሉት ቡድን እንዲቋቋም ተደርጓል፤
- ቡድኑን በማሰባሰብ ኦረንቴሽን ሰጥቶ ወደ ተሞክሮ ዝግጅት ተግባር እንዲገባ ተደርጓል፤
- የተላከውን የተሞክሮ ማዘጋጃ መመሪያ /Guideline/በአግባቡ በመገንዘብ እንደ ቡድኑ የሙያ ቅርበትና ልምድ መሰረት ርዕሶችን በመከፋፈል የተሞክሮውን ቅመራ ስራ የማከናወን ተግባር ተከናውኗል፤
- በየቡድን አባሉ በግል የተዘጋጀውን የተሞክሮ የመጀመሪያ ድራፍት በጋራ እየተወያዩ እና በመረጃ እያበለፀጉ ፅሁፉን የማጠናቀቅ ስራ ተሰርቷል፤

- በመጨረሻም የተዘጋጀውን የተሞክሮ ፅሁፍ ለአመራሩ በማቅረብ የጋራ እውቅና እንዲያዝበት የማስተካከያ ሀሳቦችም እንዲካተቱበት የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

## 1.6. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ የትኩረት መስኮች (ወሰን) ዲያስፖራው፡-

- በጎንደር ከተማ በሆቴልና ሎጂ ኢንቨስትመንት የተሳተፈበትን፤
- በጎንደር የውጭ አገር እህት ከተሞች ግንኙነት ምስረታና በግንኙነቱ በተገኙ ልዩ ልዩ ድጋፎች የነበረው ጉልህ አስተዋፅኦ፤
- በጎንደር ከተማ የጤና እና ትምህርት ልማት ዘርፍ ያደረገው አስተዋፅኦ፤
- በማህበራዊ ደህንነት ጥበቃ ላይ ያደረገው አስተዋፅኦ በቅርቡ በተካሄደው ጦርነት ምክንያት ለተሰው 29 ሰማዕታት ቤተሰቦች
    - የሁለት ዓመት ቀለብ የማመቻቸት፤
    - የልጆችን ት/ቤት ወጭና ቀለብ የመሸፈን፤
    - ልጆችን በዘላቂው ለማሳደግ ስምምነት መድረስና በባንክ አካውንት አስከፍቶ በየወሩ ገንዘብ መርዳት መጀመሩ (ለምሳሌ 5 ልጆችን ለማሳደግ ከእንግሊዝ አገር የመጡ ዲያስፖራዎች መስማማታቸው)፤
    - ለቆሰሉ በርካታ ጀግኖች በርካታ ገንዘብ ወጭ የተደረገበት (ለምሳሌ ውጭ ከሚገኙ ከአንዲት የአዘዞ የዲያስፖራ ቤተሰብ እስከ 500,000 ብር የእርድ እንሰሳትና የአልባሳት ስጦታ መደረጉ፣ የ185,000 አልባሳት ከፃዲቁ ት/ቤት የቀድሞ ተማሪ ዲያስፖራዎች ወዘተ)፤

## 1.7. የከተማው ነባራዊ ሁኔታ

### 1.7.1. የከተማው አመሰራረት (History of the city)

ጎንደር ከተማ በሀገራችን በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ከሚገኙት ቀደምት የስልጣኔ፣ የባህል፣ የቅርስ፣ የመንፈሳዊና ትውፊታዊ መገለጫዎች የመነጨባት እና ለኢትዮጵያ የከተሜነትን ትምህርት ካስተማሩና እያስተማሩ ካሉ ከተሞች መካከል ቀዳሚ ናት፡፡

ጎንደር ከተማ እ.ኤ.አ በ1624 ተመሰርታ ከ1632 እስከ 1855 ዓ.ም የኢትዮጵያ መናገሻ ወይም ዋና ከተማ ሆና ያገለገለች የከተሞች እናት ናት፡፡ ጎንደር ከተማ በአፄ ፋሲለደስ እና ሌሎች 6 ነገስታትን ጨምሮ በአሁኑ

ሰዓት የአገር የትናንት ማንነትን የሚያሳዩ እና የተደረሰበትን ስልጣኔ እስካሁን እየዘከሩ የገቢ ምንጭና የገፅታ ግንባታ ማዕከል የሆኑ የተለያዩ የነገስታት መታወሻ ግንቦችን አቅፋ የምትገኝ ከተማ ናት።

በቱሪዝም ዘርፉም ጎንደር ከተማ የእነ ፋሲለደስን አብያተ መንግስታትን አቅፋ ከመገኘት በተጨማሪ እንደ ራስ ደጀን፣ አላጣሽ የመሳሰሉ ብሄራዊ ፓርኮችን በቅርብ ርቀት የተጎራበተች በርካታ መንፈሳዊ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችም ባለቤት ናት። እነዚህንም በUNESCO በማስመዝገብ እንደ ሀገር ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው የአንበሳውን ድርሻ እያበረከተች የምትገኝ ከተማ ናት።

## 1.7.2. ከተማዋ የምትገኝበት አቅጣጫ

- ከአዲስ አበባ በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የምትገኝ ሲሆን
- ለ$12.6^0$ ላቲቲዩድ እና በ$37.4^0$ ሎንግቲዩድ የምትገኝ ከተማ ናት።
- ከአዲስ አበባ በ748 ኪ.ሜ፣ ከባህርዳር 180 ኪ.ሜ እና ከሱዳን 180 ኪ.ሜ ርቀት የምትገኝ የደረቅ ወደብ የሆነች ከተማ ናት።

## 1.7.3. የከተማው የህዝብ ብዛት

- እንደ ሀገር ወቅታዊ የሆነ የህዝብ ቆጠራ ባለመኖሩ ምክንያት ትክክለኛው ቁጥር ባይቀመጥም በአሁኑ ስዓት ከ750,000 ህዝብ በላይ የህዝብ ብዛት እንዳላት ይገመታል።
- የህዝብ ጥግግቱም 31.25 ሰው በሄክታር እንደሚሆን ይገመታል፤
- የሴትና ወንድ ንፅፅር ሲታይም 49.7% መሆኑን ሲያሳይ፤
- ከ150,000 በላይ የአባወራ / እማወራ የሚኖሩባትናት።

## 1.7.4. የከተማውዋ መሬት አቀማመጥ

- ጎንደር ከተማ ከታሪካዊ አመሰራረቷ አንፃር ሲታይ ነገስታት የመሰረቷት ስትሆን ለወታደራዊ ስልት ሲባል ዙሪያዋን ተራራማ በታ ተመርጦ የተቆረቆረች ከተማ ናት።
- ከዚህ ባሻገር ከ9 ያላነሱ ተራሮች የከበቧት ስትሆን 4 ትላልቅ ወንዞችን የያዘች ለነዋሪ የማትሰለች ከተማ ናት።
- ከመሬት ወለል በላይ ከ2000 እስከ 2200 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች።

## 1.7.5. የከተማዋ አየር ንብረት

- አብዛኛው የከተማዋ አየር ንብረት ወይናደጋማ እና የተወሰነ ሞቃታማ ነው።
- አማካኝ አመታዊ ሙቀት 19.7 ዲግሪ ሴንቲግሬድ
- አማካኝ አመታዊ የዝናብ መጠን 1,800 ሚ.ሜ ነው።

## 1.7.6. የከተማዋ የኢኮኖሚ ምንጭ

ከተማዋ ቀደምትና የንግድ ከተማ ከመሆኗ አንፃር የተለያዩ የኢኮኖሚ አማራጭ ምንጮች አሏት። እነዚህም ግብርና፣ ንግድ፣ ቱሪዝም፣ ማኑፋክቸሪንግ እና ሪሚታንስ ናቸው።

### ሀ/ ግብርና

እንደ ሀገር ግብርና የኢኮኖሚ መሰረት መሆኑን በዋነኛነት በመውሰድ ከተማዋ ግብርናን የመጀመሪያ የኢኮኖሚ ምንጭ በማድረግ እየተጠቀመችበት ይገኛል። ይህም በሁለት አማራጮች ይታያል።

### የከተማ ግብርና

በከተማዋ ያሉ አነስተኛ መሬቶችን እና የውሃ ምንጮችን በመጠቀም የከተማ ግብርና ላይ በሰፊው በመስራት የከተማው ነዋሪ የምግብ ምንጩ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ የሚሰራ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም አትክልትና ፍራፍሬ፣ የከብት ማድለብ፣ የከብት እርባታ እና የወተት ልማት፣ የዳሮ የግብርና ውጤቶችን ማልማት፣ የማር እና በገጠር ቀበሌዎችም የተለያዩ አዝዕርትን በማልማት ህዝቡን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።

### ከከተማ ውጭ ያለ መጋቢ ግብርና

ጎንደር ከተማ በዙሪያዋ ላሉ የቅርብና የሩቅ ወረዳዎች በተለይም መተማ፣ ሁመራ፣ ወልቃይት እና አለፋ የመሳሰሉት ትላልቅ የእርሻ በታዎች ማዕከል በመሆኗ እነዚህ የግብርና ምርቶች የሚከማቹባትና የሚገበያዩባት በመሆኗ ለክልሉም ብሎም ለአገር የኢኮኖሚ ምንጭ ሆና እያገለገለች ትገኛለች።

### ለ/ ንግድ

ከተማዋ ረዘም ላለ ጊዜ በንግድ ከተማነት ያገለገለች በመሆኑ በኢ-መደበኛና መደበኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች በስፋት የሚከናወኑባት ከተማ ናት።

#### ሐ/ ቱሪዝም

ከተማዋ የቱሪዝም ከተማ በመሆኗም ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ከሚመጡ ጎብኝዎች የሚገኝ ገቢ ሌላ የኢኮኖሚ ምንጭ አማራጭ ሆኖ ያገለግላል።

#### መ/ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስፋፋ ቢመጣም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከጊዜ ወደ ጊዜ የከተማው ሌላው የገቢ ምንጭ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

#### ሠ/ ወደ ሀገር የሚላክ ገቢ (Remitance)

በተለያዩ አጋጣሚዎች የከተማው እና አካባቢው ህዝብ ወደ ውጭ ሀገር በመሰደዱ ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ወደ ከተማው የሚላኩ ገንዘቦች ሌላኛው አማራጭ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

## 1.8. በከተማዋ የዲያስፖራ አካላትን በተለያዩ የልማት ስራዎች ለማሳተፍ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች (Opportunities) እና ፈታኝ ሁኔታዎች (Challenges)

### 1.8.1. ምቹ ሁኔታዎች

- በቱሪዝም ዘርፍ ከተማዋ የቱሪዝም መስህብና መዳረሻ ከተማ በመሆኗ ምክንያት ለዘርፉ ማደግ ምቹ ሁኔታ ስለፈጠረ ዲያስፖራዎች በሆቴል ቱሪዝም ልማት እንዲሳተፉ በመደረጉ ምክንያት በከተማዋ ከተገነቡ በርካታ ሆቴሎች እና ሎጂዎች ውስጥ ከ80% በላይ የሚሆኑት በዲያስፖራዎች መገንባት እንዲችሉ ያስቻለ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።
- በማህበራዊ አገልግሎትም በተለይም በት/ቤት እና በሆስፒታል ግንባታ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በመቻሉ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ፣ ግንባታ ላይ ያሉ እና የመሬት ጥያቄ ያቀረቡ በርካታ ዲያስፖራዎችን ማሳተፍ አስችሏል። (ለምሳሌ ዋሽንግተን ዲሲ በሚኖሩ እሙሃይ ኪዱ ደሴ ቤተሰቦች የቀረበው የ550 ሚሊዮን ብር የሪልስቴት ፕሮጀክት፣ የኢትዮጵያውያን እስራኤላውያን የቀረበው የ500 ሚሊዮን የባህል ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ወዘተ)

- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍም ለዲያስፖራ አካላት በተለያዩ ጊዜያት ያላቸውን እውቀትና ገንዘብ ተጠቅመው እንደ ሀገር ሰፊ ክፍተት ባለበትና የዶላር ጥያቄ በሚያበዙ ፕሮጀክቶች ላይ ተሰማርተው እንዲሰሩ ከማድረግ አንፃር በርካታ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረው በማምረቻው ዘርፍ እየተሰማሩ ያሉ ዲያስፖራዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጨምር ማድረግ ተችሏል፡፡
- በአጠቃላይ ዲያስፖራው በተለያዩ የልማት ስራዎች እንዲሳተፉ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ምክንያት ከ100 የሚበልጡ ዲያስፖራዎች በልዩ ልዩ የልማት ስራዎች አገልግሎት በመጀመር ግንባታ ላይ በመሆን እና የመሬት ጥያቄ በማቅረብ ሂደት ውስጥ ይገኛሉ፡፡

### 1.8.2. ፈታኝ ሁኔታዎች (Challenges)

ምንም እንኳን ከተማዋ ለዲያስፖራው የተሻለ እና ተደራሽነት ያለው አገልግሎት ለማቅረብ ብትሞክርም ጎን ለጎን ፈታኝ ሁኔታዎች መኖራቸው ስኬቱን እንቅፋት ፈጥረውበታል፡፡

ከእነዚህም ውስጥ፡-

ሀ/ ከ3ኛ ወገን የፀዳ መሬት አለመኖር ለሚቀርቡት የመሬት ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ እንዳይሰጥ ማድረጉ፡፡

ለ/ ከፌደራልና ክልል መንግስታት የዲያስፖራን ጉዳዮች ለማሳለጥ የበጀት እና ሌሎች ግብዓቶች ድጋፍ አለመደረጉ፡፡

ሐ/ የመሰረት ልማት አቅራቢዎች (ውሃ፣ መብራት፣ መንገድ፣ ስልክ) የተቀናጁ አለመሆን እና ለዲያስፖራዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት አለመቻሉ፡፡

መ/ የንግድ እና ገቢ ተቋማት ዘመኑን የዋጀ ብሎም ዲያስፖራው የሚኖርበትን አገር የስልጣኔ ደረጃ ያላገናዘበ ደካማ አገልግሎት አሰጣጥ መኖር ለአብነትም ቶሎ መልስ አለመስጠት፣ ማጉላላት፣ የመረጃ ፍሰት ክፍተት መኖርና ቅድሚያ አለመስጠት ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- የዝግጅት ምዕራፍ

## 2.1. የዲያስፖራ አካላትን በተለያዩ የልማት ስራዎች የማሳተፉ ዓላማ

ዲያስፖራዎች ከሚፈልጉት ነገሮች ውስጥ ዋና ዋና የሚባሉት እውቀታቸው፣ ክህሎታቸውን፣ ልምዳቸውን እና ገንዘባቸውን በማምጣት ከተማዋ ላይ ያለውን ክፍተት እንዲሞሉ ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም እንደ ጎንደር

ተጨበጭ ሁኔታ "የጥምቀትን በጎንደር" በሚል በሚካሄድ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ለመሳተፍ በየዓመቱ በጣም ብዙ ዲያስፖራዎች ወደ ከተማዋ የሚመጡ በመሆኑ እስከ አሁን ወደ 8 አመታዊ የዲያስፖራ ፎረሞች የተካሄዱ ሲሆን በዚህም የከተማዋን የመልማት አቅም በማሳየት የበለጠ እንዲሰሩ የማድረግ አላማን ይዞ እየተሰራ ይገኛል። በዚህም በቅርቡ የከተማ አስተዳደሩ በማኑፋክቸሪንግ፣ በሪልስቴት፣ ሆቴልና ቱሪዝም እና ማህበራዊ ዘርፍ እንዲሰማሩ ፕሮጀክታቸውን የማፅደቅና መሬት የመስጠት ስራዎች ተሰርተዋል።

## 2.2. የዲያስፖራ አካላትን በዘላቂ የልማት ስራዎች ለማሳተፍ ካለ ዝግጅት አንፃር

**2.2.1.** ከአገር ውጭ ከተማው በፈጠረው የከተሞች እህትማማችነት ግንኙነት ስምምነት እና በአገር ውስጥም በተደጋጋሚ በተካሄዱት በርካታ የዲያስፖራ ፎረሞች አበረታች ውጤት የሚያስገኙ ተግባራት ተከናውነዋል። ለመጥቀስ ያህልም፡-

ሀ/ በታላቁ ወደ ሀገር መምጣት ጥሪ ላይ እንደ ከተማ ወደ መሬት የወረደ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ዲያስፖራውን የሚስቡ አገሩንና ከተማውን እንዲያለማ የሚያበረታቱ ልዩ ልዩ ሁነቶች ተከናውነዋል። ለምሳሌ፡- የዲያስፖራ የምስጋና ፕሮግራም፣ በባህል ዝግጅት የታጀበ የንጉስ እራት ፕሮግራም፣ የንግድ ትርኢትና ባዛር ፕሮግራም፣ የጎርጎራ፣ ዳንሻ ሁመራ ጉብኝት ፕሮግራም፣ የሆቴሎች እና ፋብሪካዎች ምረቃ ፕሮግራምና የፓናል ውይይት ፕሮግራም።

ለ/ ከተማዋ ለኢንቨስትመንት ያላትን ምቹነት በተግባር የማሳየት ዝግጅትና በመስክ ምልከታ የተደገፈ ስራ ተሰርቷል።

ሐ/ ዲያስፖራዎችን ኤርፖርት ድረስ ሄዶ በባህላዊ ቡና የማጠጣት እና የባህል ጭፈራ የታጀበ አቀባበል እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሆቴል ወይም አካባቢ እንዲያርፉ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

መ/ በቀጣይ ትኩረት አድርገው ስለሚሰሩባቸው የቀጥታ ኢንቨስትመንቶች፣ የጎርጎራ ፕሮጀክት እና የመገጭ ግድብን ለኢንቨስትመንታቸው የትኩረት አቅጣጫ እንዲያደርጉት የሚያሳይ የዝግጅት እና ጉብኝት ስራ ተሰርቷል።

### 2.2.2. የእውቀትና የክህሎት ሽግግር ከማድረግ አኳያ

ከትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሚፈልጉት ነገሮች ውስጥ የእውቀትና የክህሎት ሽግግር ማድረግ አንዱና ዋናው የዝግጅት ስራ ነበር። በዚህም በተለይ በከተማዋ እየተስተዋለ ያለውን የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ችግር ለማቃለል እንዲረዳ ዲያስፖራዎች ያላቸውን እውቀት ክህሎት ለመጠቀም ያመች ዘንድ እንደየ ዲያስፖራዎች እውቀትና ክህሎት ለመጠቀም በተለይም በሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ እየሰሩ ያሉ ባለሙያዎችን በቀጣይ ለመጠቀም የሚያስችል ስምምነት እና መግባባት ስራ ተሰርቷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በሲያትል የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ያቋቋሙት MMRTI (multi media and resource technology institute)የተሰኘ ድርጅት ዲጅታል ሚዲያና ቴክኖሎጅ ሴንተር በከተማችን ለማቋቋም በዚህ ወቅት እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ይህም ቋሚ ቦታ እስክንሰጠው ድረስ በጎንደር ከተማ ህዝብ ቤተ-መጻህፍት አንድ ሰፊ ክፍል ተሰጥቶት ስራ ለመጀምር በዝግጅት ላይ ይገኛል።ይኸው ተቋም 200 ለሚሆኑ የከተማችን ወጣቶች ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመገናኘት ዘመኑ የደረሰባቸው የፎቶግራፍ እና የቪዲዮ ካሜራዎችን አጠቃቀም ስልጠና በመስጠት የመረጃ አያያዝ አቅምን በማጎለበት እንዲሁም የማህበራዊ ድህረ ገጾችን በአግባቡ ተጠቅሞ ሀብት እንዴት ማመንጨት እንደሚቻል ግንዛቤ ፈጥሯል። ዘመናዊ የሚዲያ መገልገያ መሳሪያዎች ማለትም መቅረጸ ደምጽ፣ ዘመናዊ ቪዲዮ ካሜራዎችን ልዩ ልዩ ምስልና ድምጽ ማቀናበሪያ ኮምፒውተሮችና ሶፍትዌሮች በስጦታ አበርክቷል።

የጎንደር የህዝብ ቤተ-መጻህፍት ቴክኖሎጅን መሰረት ያደረገ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል በጋራ እየሰራን እንገኛለን። በጥር 2013 ዓ.ም በተደረገው የጥምቀት ዲያሥፖራ ፎረም ላይ የተሳተፉት የሶፍትዌር ኢንጂነሩ ሀብታሙ አሰፋ በጋለ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ እና በከንቲባ ፅ/ቤት መካከል ያለውን የኢንቨስትመንት መረጃ ልውውጥ ከወረቀት ወደ ኮምፒውተራይዝድ ስራ ለመቀየር ሶፍትዌር በማበልፀግ ላይ ሲገኙ ይህንም ከምክትል ከንቲባው፣ ከኢንቨስትመንትና ከከንቲባ ከፍተኛ ባለሙያዎች ጋር የመረጃ (Data input)ልውውጥ እያደረጉና ስራውን ወደ መሬት ለማውረድ በራሳቸው ባለሙያዎችን ቀጥረው እየሰሩ መገኘታቸው እንዲሁም በጥር 2014 ዓ.ም የጥምቀት ዲያስፖራ ፎረም ደግሞ በሲያትል የሚገኙት እና በማይክሮሶፍት ካምፓኒ የሚሰሩት ኢንጂነር ኢሳያስ ከተማዋ በቴክኖሎጂ ታግዛ በመስራት መቅረፍ የምትፈልግው ስራ ካለ የቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማድረግ በይፋ ከተማው ችግሩን ለይቶ እንዲያሳውቃቸውና አስፈላጊውን ሶፍትዌር አበልፅገው እንደሚያበረክቱ ተናግረዋል። ይህም ዲያስፖራው በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያለውን የማይተካ ሚና የሚያሳይ በተጨባጭ የታየ ተሞክሮ ነው።

### 2.2.3አካባቢን መሰረት አድርጎ ማህበራትን በማቋቋምና ስደተኞችን እና ከስደት ተመላሾችን መልሶ ለማቋቋም ሃብት በማሰባሰብ በኩል ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ

በታላቁ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ፕሮግራም ጋር ተያይዞ ዲያስፖራው ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት በገንዘብና በቁሳቁስ በተለይም በምግብና በህክምና ዕቃዎች ላይ ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስቻለ በርካታ ስራ የተሰራበት ነው፡፡ የጎንደርና ዙሪያው አካባቢ ተወላጆች ዲያስፖራዎች ተፈናቃዮች አሉበት አካባቢ ድረስ እየሄዱ (ለምሳሌ ከአሜሪካና ካናዳ ተደራጅተው የመጡ ዲያስፖራዎች በርካታ ሚሊየን ብር በመመደብ በጎንደር፣ በደባርቅና በእብናት እንዲሁም በደብረ ብርሃን ለተፈናቃይ ወገኖች በጥሬ ገንዘብና የአይነት ድጋፎችን ማድረጋቸው፣ ደጀን ኢትዮጵያ የተባለው የዲያስፖራ ማህበር በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ መድቦ ለህልውና ዘመቻው የፀጥታ ሀይልና ለተፈናቃዮች በየግንባሩ ለምሳሌ በደሴ፣ በእብናትና በደባርቅ በመገኘት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ መድቦ ተከታታይ የምግብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረጉ እንዲሁም ሌሎች የጎንደርና አካባቢው ተወላጆች ዲያስፖራዎች ለተፈናቃዮችና ለፀጥታ ሀይሉ በአይሱዙዎች የተጫነ በርካታ ጫማ፣ አልባሳትና መድሃኒት እንዲሁም ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህክምና ቁሳቁሶች ለምሳሌ፡- ስቴትስኮፖች ድጋፍ መደረጉ አሜሪካን አገር የሙሃይ ኪዴ ደሴ ቤተሰብ 10 ሚሊየን ብርና 150 የተለያዩ እንሰሳት ለተፈናቃዮችና ለፀጥታ ሀይ ወዘተ ድጋፍ ማድረጋቸው)፡፡ በቀጣይም በየመጡበት አካባቢ ተደራጅተው ዘላቂነት ያለው ድጋፍ እንዲያደርጉ በማወያየትና ላልመጡት የዲያስፖራ ማህበረሰብም ጥሪ የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

### 2.2.4.ቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ከማሳደግ አኳያ

የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ በዋናነት ሶስት ነገሮች Amenity Accommodation Accessibilityሊሟሉ ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም የአገልግሎት ዘርፉ ማለትም Accommodation አንዱ የቱሪዝም ምሰሶ ነው፡፡ የግል ባለ ሐብቱ በስፋት ሊሳተፍበት የሚችለውና የሚገባው በዚህ ዘርፍ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሰረታዊ ልማት ዘርፍ ከተማችን ላይ ያለውን ምቹ ሁኔታ አስመልክቶ ዲያስፖራው ግንዛቤ እንዲኖረው በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በመዘዋወር ከፍተኛ ስራ የተሰራ በመሆኑ በከተማችን ላይ አይነተኛ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ ለምሳሌ፡-

ሀ/ በከተማችን ካሉ 12 ባለ ኮከብ ሆቴሎች 10 በዲያስፖራው የተገነቡና ወደ አገልግሎት የገቡ ናቸው፡፡

ለ/ በከተማችን ካሉ 18 ቱሪስት የሚመጥን ሆቴሎች 11 በዲያስፖራው ተገንብተው ወደ ስራ የገቡ ናቸው።

ሐ/ ካሉን 6 ኮከብ ደረጃ የሚይዙ ሎጆች ውስጥ 3 በዲያስፖራ የተገነቡና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ናቸው።

## በማህበራዊ ልማት የዲያስፖራው ተሳትፎ

በማህበራዊ ልማት የዲያስፖራው ተሳትፎ እጅግ ጉልህ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። በተለይም በትምህርት እና በጤና በእጅ ሊዳሰሱ የሚችሉ የልማት ስራዎች ተከናውነዋል። ለአብነት፡-

### በትምህርት

1. ቀይ አምባ ትምህርት ቤት ላይ እያንዳንዱ 6 የመማሪያ ከፍሎች ያሉት ሶስት ብሎኮችን በመገንባት አገልግሎት ላይ አውለዋል።
2. ቴኬርኦፍ ተብሎ የሚጠራ የጎንደር አካባቢ ተወላጆች ማህበር አዘዞ ጠዳ ክ/ከተማ _የመማሪያ ክፍሎች ያሉት 2 ብሎኮች በመገንባት ትምርት ቤት ማስፋፊያ ስራ ላይ በመሳተፍ ላይ ነው።
3. ቀበሌ 3 አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የክፍል ጥበት ችግር ለማቃለል 2 ብሎክ 8 የመማሪያ ክፍል ያሉት እየተገነባ ይገኛል።
4. ፋሲለደስ ፕሪፓራቶሪ ት/ቤት ለጊዜው በ G+2 ደረጃ በመገንባት ላይ ያለው 34 የመማሪያ ክፍሎች 10 የአስተዳደር፣ የላይበራሪ … ወዘተ ክፍሎች ያሉት ህንጻ ሙሉ በሙሉ ወጭው በዲያስፖራው ማህበረሰብ ተሸፍኖ በመከናወን ላይ ይገኛል።

### በጤና

1. በአሜሪካ፣ በአውሮፓና ስፔን የሚኖሩ የጎንደር ተወላጅ ኢትዮጵያዊያን የተገነባ ዘመናዊ የጽንስ ክትትልና ማዋለጀ ተቋም
2. ለዚሁ የጤና ማዕከልና ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል በስጦታ የተለገሱ በርከታ ዘመናዊ የህክምና መስጫ አልጋዎችና 6 አምቡላንሶች፤
3. የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማችን ተከስቶ አለምን እያተራመሰ ባለበት በዚህ ወቅት በቁጥር ለመግለጽ አዳጋች የሆነ የጤና ሰራተኞች ጋውን፣ ሳኒታይዘር፣ የፊት ጭንብል እና ሌሎች የህክምና መርጃ መሳሪያዎች በስጦታ አበርክተዋል፣ እያበረከቱም ይገኛሉ።
4. ለጎንደር ፖሊ ክሊኒክ ልዩ ልዩ የህክምና መርጃ መሳሪያዎች ድጋፍ አድርገዋል።

## 2.2.5. የእህትማማች ከተሞች ትስስርና ትብብርን ለመፍጠር ዲያስፖራው የሚያደርገው ድጋፍ

ያደጉት አገራት ከተሞች በሁሉም መስክ በሚባል ደረጃ ሊቀሰም የሚችል ተሞክሮ እንዳላቸው እሙን ነው። ስለሆነም ከከተሞች ጋር ትብብርና ትስስር መፍጠር ለከተማ እድገት ያለው ፋይዳ ጉልህ ነው። ከዚህም የተነሳ የጎንደር ከተማ አስተዳደር ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ተግባሩም የተሳካ ይሆን ዘንድ በበርከታ ጉዳዮች የምንመሳሰላቸው ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ የጎንደር እና አካበቢው ተወላጅ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሚኖሩባቸው የውጭ አገር ከከተሞች ጋር በእህትማማችነት እንድንቀራረብ አድርገዋል።

### እነዚህም፡-

- ጎንደር- ቬንሰሰ ፈረንሳይ እህትማማች ከተሞች ግንኙነት፣
- ጎንደር-ሞንቶጎሞሬ ካውንቲ ሜሪላንድ አሜሪካ እህትማማች ከተሞች ግንኙነት፣
- ጎንደር-ኮርቫሊስ ኦሪገን አሜሪካ እህትማማች ከተሞች ግንኙነት፣
- ጎንደር-ሪሾንለጺዮን እስራኤል እህትማማች ከተሞች ግንኙነት መመሰረት ላይ የማይተካ ሚና ተጫውተዋል።
- ከአውሮፓ ህብረት እና ከጃፓን ኦዳ ከተማ ጋር ትብብር እንዲኖረን አስችለዋል።

### ከዚህ ግንኙነት ከተማችን በርካታ ጥቅሞችን አግኝታለች፡-

- በእንግሊዝ አገር ዊንድሶር ከተማ የሙያተኞችና አመራሮች ልምድ ልውውጥ እና ስልጠና፤
- በከተማችን ተደራጅተው ለሚሰሩ የፎቶግራፍ አንሽዎች የሙያ ስልጠና፤
- ከቤንሰስ እህት ከተማ ወደ 22 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ በማግኘት 16ኛው ክ/ዘመን የተገነባውን የራስ ግንብ ህንጻ ሙሉ እድሳት እንዲደረግለት በማድረግ ወደ ታሪካዊ ሙዚየምነት እንዲቀየር ተደርጓል፤
- ከአውሮፓ ህብረት በተገኘ 15 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ የጎንደር ባህል ማዕከልና የፋሲለደስ የባህል ቡድን ተቋቁሞ ስራ እንዲጀምር ዘመናዊ የድምጽ ግብዓት መሳሪያዎች ግዥ፣ የጎንደር ሲኒማ ቤት ጥገናና ለባህል ቡድኑ መንቀሳቀሻ የሚሆን ዘመናዊ አውቶብስ እንዲሟላ ተደርጓል፤
- በኮርቫሊስ ኦሪገን ከተማ ድጋፍ የችግኝ ማፍያ ጣቢያ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን ለአካባቢው ገበሬ የችግኝ አቅርቦት እንዲያገኝ በማድረግ እንዲሁም የአፈር መሸርሸርን በመግታት የአካባቢው ስነ-

ምህዳር እንዲጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ። ከዚህ የእህትማማች ግንኑነትና በዚሁም ምክንያት በተፈጠሩ ሌሎች የድርጅት፣ የማህበር ወዘተ ግንኙነቶች ለትምህርት ተቋማት፣ ለጤና ተቋማት፣ ለውሃ ተቋማት፣ ለአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ወዘተ ስራዎች ወደ 85 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የቁሳቁስ ድጋፍና ወደ 65 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ ተገኝቷል። (ለምሳሌ 17,500,000 የጎንደር ሳይን ማዕከል ግንባታ፣ የ122,000 ዶላር የአብዮት ፍሬ ት/ቤት የG+1 የ10 የመማሪያ ክፍል ግንባታ፣ ከ150 በላይ ለት/ቤትና ሆስፒታል ኮምፒውተሮች የተለያዩ የህክምና ማሽኖችና መሳሪያዎች፣ በሽዎች የሚቆጠሩ ዋቢ መፃህፍትና ጆርናሎች፣ በሽዎች የሚቆጠሩ የስፖርት ትጥቆች፣ የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ግምባታዎች፣ የአካባቢ ጥበቃ አመታዊ በጀት የመመደብና የሙያተኛ ድጋፍ የመስጠት)

## 2.2.6.ለዲያስፖራው ያሉ ዕድሎችን፣ ፍላጎትና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዎችን አስመልክቶ መረጃ መስጠትን በተመለከተ

በዚህ በኩል በርካታ ዝግጅቶች የተደረጉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም የተለያዩ ሰነዶችን በማዘጋጀት ግንዛቤ በተከታታይ ለመፍጠር ተሞክሯል።

### 1.ለዲያስፖራው ያሉ እድሎች

ዲያስፖራው በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዳሉት ለማሳየት የተሞከረ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም በተለይም የአገር ውስጥ ነዋሪ ባለሀብቶች ሊገቡባቸውበማይችሉ እና የዶላር ምንዛሬ በሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶችእንዲሳተፉ ቅድሚያ የመስጠት ዕድሎች የተመቻቹ ሲሆን በእነዚህም፡-

- የህክምና ዕቃዎችን እና መድሃኒቶችን ማምረት፤
- የእርሻ መሳሪያዎችን ማምረት፤
- የኬሚካል ውጤቶችን ማምረት፤
- የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶችን ማምረት ሲሆን በአገልግሎት ዘርፉም በሪልስቴት ባለ ኮከብ ሆቴሎች ላይ እንዲሳተፉ ዕድሎችን ማመቻቸት ተችሏል።

### 2. ፍላጎታቸውን ከማሳካት አንፃር

እንደ ከተማ የተዘጋጁ ዕድሎችን እንዲጠቀሙ ከተመቻቸው በተጨማሪ ዲያስፖራዎቹ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት መነሻ በማድረግ በራሳቸው ፍላጎት መሰረት የሚፈልጓቸው ላይ መስራት

እንዲችሉ በዚህም በሚፈልጉት ተቋም ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ እና ስብስብ አድርጎ ለማስተናገድ የሚያስችል ዝግጅት በማድረግ ለመስራት ተሞክሯል።

## 3.ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዎችን መረጃ መስጠትን በተመለከተ

ከዚህ አኳያ ሰፊ ስራ የተሰራ ሲሆን በዚህም በአንድ በኩል ምን ዓይነት ፈተና ሊገጥማቸው እንደሚችል ቀድሞ በመገንዘብ እና በመለየት ይህንንም ችግሮችን ለዲያስፖራዎቹ በማስረዳትና መረጃ በመስጠት መሰል ችግር እንዳይገጥማቸው መረጃ የመስጠት ስራ ተሰርቷል። በዚህም፡-

ሀ/ ዲያስፖራዎቹ በተናጠል ማከናወን በማይችሏቸው ፕሮጀክቶች ላይ በማህበር በማደራጀት ያለባቸውን የገንዘብ እና የጊዜ ችግሮችን እንዲፈቱ ለማድረግ ተሞክሯል።

ለ/ በአገር ውስጥ የሚኖራቸው ቆይታ አጭር ጊዜ ስለሚሆን የልማት ጥያቄዎቻቸው ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ አገር ውስጥ ማስቀጠል የሚችሏቸውን ስራ እንዲሰሩ እና ወደ ውጭ አገር ሲመለሱ ግን ውክልና መስጠት ለሚችሉት አካል ውክልና እንዲሰጡ በማድረግ ችግሩ እንዲቀረፍ ለማድረግ ተሞክሯል።

ሐ/ በሌላ በኩል ሊገጥሙ ከሚችሉት ችግሮች ውስጥ አንዱ ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ መለዋወጫ ስርዓት አለመኖር ሲሆን ይህ ችግር ላለው የልማት እንቅስቃሴ ማነቆ መሆኑን በማስረዳት የጋራ እና የተናጠል የመረጃ መለዋወጫ መንገድ መፍጠር ተገቢ መሆኑን በማስረዳትና መረጃ በመስጠት ዘላቂ መፍትሄ እንዲኖር ለማድረግ ተሞክሯል።

## ምዕራፍ ሶስት፡- የትግበራ ምዕራፍ

### 3.1. የአፈፃፀም ስርዓትና አደረጃጀት

- እንደ ጎንደር ከተማ የዲያስፖራውን ተሳትፎ ለማጠናከር መጀመሪያ በውጭ አገር በተለይም አውሮፓ፣ አሜሪካ እና እስራኤል የሚኖሩ የጎንደር ከተማና አካባቢው ተወላጅ ዲያስፖራዎች ጋር ጎንደር በሚኖሩ ቤተሰቦቻቸው አማካኝነት ግንኙነት የመፍጠር ስራ እንዲሰራ ተደርጓል።
- ዲያስፖራዎቹም የሚኖሩባቸውን የከተማ አስተዳደሮች በመጠየቅና በማግባባት ስለጎንደር ከተማ የተዘጋጀውን የከተማዋ ፕሮፋይል በማቅረብ የእህት ከተሞች ግንኙነት እንዲመሰረት መደረጉ። (ለምሳሌ የጎንደር ኮርቫለስኦሪገን-አሜሪካ እህትማማች ከተሞች ግንኙነት፣ የጎንደር ሪሾን ለፅዮን-እስራኤል እህትማማች ከተሞች ግንኙነት የጎንደር-ሞንትጎመሪ ካውንቲ-ሜሪላንድ/አሜሪካ እህትማማች ከተሞች ግንኙነት የጎንደር ቬንሰንስ ፈረንሳይ እህትማማች ከተሞች ግንኙነት እንዲመሰረት መደረጉ)
- በኢትዮጵያ ሚሊኒየም የ2000 በርካታ የጎንደርና አካባቢው ተወላጅ ዲያስፖራዎች ወደ ጎንደር በመጡ ጊዜ በርካቶችን አሰባስቦ በማወያየት በሊዝ ስርዓት የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ እና የመኖሪያ ቤት እንዲሰሩ እንዲሁም በልዩ ልዩ ኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲሰማሩ መደረጉ፤
- ከኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር ጋር ተያይዞ ሲሰራ ከነበረው ስራ እና የጎንደር እህትማማች ከተሞች ግንኙነትን ለማስቀጠል የሚያገለግል በሰው ሃይልና በቁሳቁስ የተደራጀ የስራ ክፍል በጊዜያዊነት እንዲቋቋም መደረጉ (ከ2000-2005)

ከዚህ ጋር ተያይዞም አደረጃጀቱን አጠናክሮና አስፋፍቶ ማስቀጠል እንዲቻል

- የፋሲለደስ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር በአሜሪካ፣ ካናዳ
- የጻዲቁ ዮሐንስ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር በአሜሪካ ዋሽንግተን
- የጎንደር እና አካበቢው ተወላጆች ማህበር በካናዳ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

  እነዚህ አደረጃጀቶች ከጽ/ቤቱ ጋር እንዲተሳሰሩ የተደረገ በመሆኑ አደረጃጀቱን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት ተደርጓል።

## 3.2. የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት

ከሚሊኒየም ቀደም ብሎ በሚሊኒየም አከባበር ወቅትና ከዚያ በኋላ ባሉት ጥቂት አመታት ከዲያስፖራው ጋር የተደረገው ግንኙነት እና በጥቂቱም ቢሆን ዲያስፖራው የተሳተፈባቸውን የልማትና የእህት ከተሞች ግንኙነት እንዲሁም ከግንኙነቱ የተገኙ ጥቅሞች በስራ ክፍል እና በከተማ አስተዳደር ካቢኔ ደረጃ የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ወቅታዊ ግምገማና የማጠናከሪያ አሰራሮች ሲከናወኑ ቆይተዋል። ከእነዚህም ተግባራት አፈፃፀም አልፎ አልፎ በከተማው ምክር ቤት ደረጃ እየቀረበ የጋራ እውቅና እንዲያዝበት ይደረግ ነበር።

## 3.3. ተሞክሮው ያመጣው ተፅዕኖ ወይም ፋይዳ

- ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያ 2000 ሚሊኒየምና የዲያስፖራ ማስተባበሪያ ክፍል ስራውን አጠናቅቆ በ2005 ከተዘጋ በኋላ የውጭ ግንኙነቱ ያስገኘውን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ማስቀጠል እንዲቻል ስራውም ፈፅሞ እንዳይቆም አንድ ሙያተኛ ከመደበኛ ስራው በተጨማሪ የእህት ከተሞች ግንኙነትን እና የዲያስፖራ ጉዳዮችን እንዲያስተባብር ተመድቦ ሲሰራ መቆየቱ።
- ከባለፉት አመታት ከተገኙ መልካም ተሞክሮዎች መነሻነት በ2009 ዓ.ም የእህትከተሞችን ግንኙነትና ከመንግስት መደበኛ በጀት ውጭ ሊገኙ የሚችሉ የልማት ድጋፎችን በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ ለማሰባሰብና ስራ ላይ ለማዋል እንዲቻል እንዲሁም የዲያስፖራ ግንኙነቶችን እና በዛ በኩል የሚደረጉ የልማት ጥረቶችን የሚያሳልጥ እና የሚያስተባብር የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ዩኒት ማቋቋም የሚያስችል ጥናታዊ ፕሮፖዛል እንዲዘጋጅ ከዲያስፖራ አባላትና አዲስ አበባ ከሚገኙ የአካባቢው ተወላጆች በቀረበው አስተያየት መሰረት በ2010 ዓ.ም የፕሮጀክት ዩኒት ማቋቋሚያ ፕሮፖዛሉ ተዘጋጅቶ መጀመሪያ በከተማው አስተዳደር ካቢኔ ደረጃ እንዲታይ ከተደረገ በኋላ በዛው

ዓመት ለከተማው ምክር ቤት እንዲቀርብ ተደርጎ የማቋቋሚያ ደንብ እንዲወጣለት ከምክር ቤቱ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የማቋቋሚያ ደንቡ ወጥቶ መፅደቅ ችሏል፡፡

- የፕሮጀክት ዩኒቱም በከንቲባ ፅ/ቤቱ ስር ለከንቲባው ተጠሪ ሆኖ እንዲቋቋም ተወሰነ፡፡
- ከሁለት ዓመታት በኋላ በግንቦት 2013 ዓ.ም **የትበልፅግ ጎንደር የፕሮጀክት ዩኒት** እራሱን ችሎ በሰው ሃይልና በበጀት ተጠናክሮ እንዲቋቋም ተደርጎ በአሁኑ ጊዜ የጎንደር ከተማን ልማት የሚደግፍ የተጨማሪ ሀብት ማመንጨትና የጎንደር ከተማ የእህትማማች ከተሞችን ግንኙነት የማስተባበር እንዲሁም የከተማዋን የዲያስፖራ እና የውጭ ግንኙነት ተግባራትእንዲጎለብቱ እንዲሁም በከተማዋ ልማት ላይ የዲያስፖራው ተሳትፎ እንዲጠናከር የሚያስችል የህዝብ ግንኙነት ስራን አጠናክሮ እያከናወነ ይገኛል፡፡

### 3.3.1. አወንታዊ ፋይዳ

የልዩ ድጋፍ ፕሮጀክት ሀብት ማመንጫያ እና የእህት ከተሞች ግንኙነት ማስተባበሪያ ስራው ለከተማው በገንዘብና ቁሳቁስ ያስገኘው ድጋፍ በጣም ጥሩ የሚባል በመሆኑ ከ1997-2012 በጥሬ ገንዘብ ከ60-65 ሚሊዮን በቁሳቁስ ግምቱ 85 ሚሊዮን የሚደርስ ሃብት ማስገኘቱን ግምት ውስጥ በማስገባት የነበረውን ጥረት ለማጠናከርና ለማስፋፋት እንዲቻል በሰው ሃይልና በበጀት የተጠናከረ የትበልፅግ ጎንደር የፕሮጀክት ዩኒት እንዲቋቋምና ተግባሩን እንዲያከናውን መደረጉ የተሞክሮው አወንታዊ ፋይዳ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

### 3.3.2. ተሞክሮው የተሻለ አንፃራዊ የአፈፃፀም ደረጃ ማስመዝገቡን በተመለከተ

- ያለፈውን ተሞክሮ ገምግሞና ቀምሮ የተሻለና እራሱን ችሎ የሚሰራ የስራ ክፍል (**ትበልፅግ ጎንደር ፕሮጀክት ዩኒት**) ከተቋቋመና ወደ ስራ ከገባ ጥቂት ወራት ያስቆጠረ ከመሆኑም በላይ ከህልውና ማስከበር ዘመቻና ከሰላምና መረጋጋት ጋር ተያይዞ በሙሉ ትኩረት ለመንቀሳቀስ ተፅዕኖ ያጋጠመው ቢሆንም በተቆራረጠ ሁኔታም ውስጥ በተከናወኑ ተግባራት አበረታች ውጤት ማስመዝገብችሏል፡፡ (ለምሳሌ ባለፉት ሁለት ወራት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማወያየትና በማግባባት ለሰብዓዊ ድጋፍ አገልግሎት የሚውል የ1.45 ሚሊዮን ብር የምግብና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም 2.41 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የ200 አልጋና ፍራሽ ድጋፍ እንዲገኝ የማድረግ ስራ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡)
- በአጠቃላይግን ተሞክሮው የተሻለ አንፃራዊ የአፈፃፀም ደረጃ ማስመዝገቡን ለማሳካት ቀጣይ ያሉ የስራ ጊዜያትን በአግባቡ መጠቀም የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

## 3.4. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

### ሀ. ውጫዊ ችግሮች

- በውጭ የሚገኙ የዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላትም ሆኑ የእህት ከተሞች ግንኙነት አስተባባሪ ዲያስፖራዎች በግል ጉዳያቸው የመጠመድ አንዳንዴም ትኩረት ያለመስጠት ወይም ስራውን ተከታታይ ከማድረግ ይልቅ የተቆራረጠና ወቅታዊ የማድረግ አዝማሚያ ማመዘኑ፤
- በዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላት መካከል ያለመግባባት መፈጠር አንዳንዴም የመንደርተኝነት እና የቡድንተኝነት አዝማሚያዎች መከሰታቸው፤
- በዲያስፖራ አስተባባሪዎች በኩል የተጠናከረ የዶክሜንቴሽንና፣ የመረጃ ማደራጀትና ሪፖርት የማድረግ ልምድ አናሳ የነበር መሆኑ፤
- እንደ አገር ዲያስፖራው በልማት፣ በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ እንዲሳተፍ በመንግስት የሚደረገው ጥረት እጅግ አናሳና የማያበረታታ የነበር መሆኑ፤
- ወቅታዊ አገራዊ አለመረጋጋት እና ኮቪድ 19 የፈጠሩት ተፅዕኖ መኖር።

### ለ.ውስጣዊ ችግሮች

- ግንኙነቱን በማጠናከር በኩል ከፍተኛ ድርሻ የሚጠበቅባቸው የከተማው ከንቲባዎች በጣም አጭር ጊዜ በሚባል ሁኔታ በተደጋጋሚ ጊዜ ከቦታው መነሳታቸው። (አንዳንዴም አዲስ የተሾመውን ከንቲባ ለውጭው ማህበረሰብ አስተዋውቀን ሳንጨርስ የከንቲባውን ከቦታው መነሳት ለመግለፅ መገደድ)። ይህም በውጭው የዲያስፖራማህበረሰብ ላይም ሆነ ሌሎች የልማት አጋሮች ላይ የሚፈጥረው መደነጋገር/ ግራ መጋባት ከአዲሱ ሀላፊ ጋር እንደገና ከባዶ /ዞሮ የመጀመር ነገር የጎላ ችግር ሆኖ መቀጠሉ፤
- አንዳንዴ በከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮችና ተቋሞቻቸው በኩል ለስራው ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት እንዲያውም ከውጭው ዲያስፖራም ሆነ የውጭ ዜጎች ጋር እየተገናኙ መስራት የቅንጦት ወይም የተለየ ግላዊ ጥቅም የሚያስገኝ ተደርጎ መታየቱ፤
- ለስራ ክፍሉ መጠናከር የሚያስፈልግ የሰው ሃይልም ሆነ በጀት እና ቁሳቁስ አለመመደብ፤
- የውጭው ዲያስፖራም ሆነ የውጭ ዜጎች ለከተማው ለሚያደርጉት ድጋፍ ወቅቱን የጠበቀና ድጋፉን የሚመጥን የምስጋናም ሆነ የእውቅና ፕሮግራም አለማዘጋጀት ወይም በፅሁፍ በምስክር ወረቀት እውቅና አለመስጠት።

## 3.5. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች

- የውጭ ግንኙነት የሚያስተባብሩ ዲያስፖራችን እየለዋወጡ/እያተካኩ ለመስራት መሞከር፤
- የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራር ለውጭ ግንኙነት ስራው ተገቢ ትኩረት እንዲሰጥ ጉዳዩ በምክር ቤት ደረጃ እንዲቀርብና ለስራው መዳከም ማብራሪያ እንዲሰጥበት የማድረግና ለችግሩ ባለቤት የመስጠት እና ተጠያቂ የማድረግአሰራርን መከተል መቻሉ፤
- ከውጭው ዲያስፖራና የውጭ እህትማማች ከተሞች ግንኙነት አስተባባሪ አካላት ጋር በመነጋገርና በማሳመን የከተማው ከፍተኛ አመራሮች የውጭ ጉብኝት ፕሮግራም እንዲዘጋጅ በማድረግ የልምድ ልውውጥ ተግባር አከናውነው እንዲመለሱ መደረጉ፤
- አሜሪካ ወደ 3 ጊዜ እስራኤል ወደ 3 ጊዜ፣ ፈረንሳይ 1 ጊዜ የጉብኝት እና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራም መካሄዱ።

## 3.6. የተገኙ ውጤቶች /ተሞክሮዎች

- የዲያስፖራ ግንኙነቱን ሆነ የውጭ አገር እህትማማች ግንኙነቱን የሚያስተባብሩት አካላት አመለካከት ቀስ በቀስ እየተስተካከለ እና አገርና ወገንን ማገልገል ያለውን ክብርና ጥቅም እያስተዋሉት መምጣታቸው እና ከትርፍ ጊዜም በላይ ወሳኝ ጊዜያቸውን እና የግል ንብረታቸውን ለዚሁ ግንኙነት መጠናከር ማዋል መጀመራቸው፤
- የከተማው ከፍተኛ አመራሮች ከውጭ አገር ጉብኝት እና እግረ መንገዱን ከተካሄዱ የልምድ ልውውጦች በኋላ ለስራው ተገቢ ትኩረት በመስጠታቸው የዲያስፖራና የውጭ እህት ከተሞች ግንኑነት ማስተባበሪያ እንዲሁም ተጨማሪ የልማት ሃብት ማመንጪያ የስራ ክፍል በሰው ሃይልና በበጀት ተጠናክሮ እንዲደራጅና ወደ ስራ እንዲገባ መደረጉ፤

# ምዕራፍ አራት

## 4.1. ዲያስፖራ አካላትን በልማት ስራዎች የማሳተፍ ስራው ቀጣይነት ያለው

## ስለመሆኑ

እንደ ጎንደር ያሉ ከተሞች አንደኛው የገቢ ምንጫቸው የሆነው ኢንቨስትመንቱ ተስፋፍቶ እንዲቀጥል ምቹ ሁኔታ ከሚባለው አቅም ዋነኛው በርከት ያለ የዲያስፖራ ቁጥር መኖሩ ነው።

ስለሆነም ይህን መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ እስካሁን በነበረው ጊዜ ባለመሰራቱ ምክንያት ከተማዋ መጠቀም የሚገባትን የልማት ትሩፋት ሳታገኝ ቆይታለች። ይህን ድክመት እንደ ትምህርት በመውሰድ የዲያስፖራ አካላት ቀጣይነት ባለው የልማት ስራዎች እንዲሳተፉ ስልት በመቀየስ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ይዋል ይደር የሚባል ጉዳይ አይደለም።

ከዚህ በመነሳትም በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን እነዚህን ማስቀጠል ዋና አጀንዳ ተደርጎ ተይዞ እየተሰራበት ይገኛል።

ሀ/ ላለፉት 8 ዓመታት በየዓመቱ ይካሄድ የነበረውን የጥምቀትን የዲያስፖራ ፎረም በማስቀጠል ነባሮች እንዲበረቱ እና አዲሶችም ወደ ልማት እንዲገቡ የማድረጉ የቀጠለና ለወደፊቱም የሚቀጥል መሆኑ።

ለ/ ከተማው ከባለፉት 16 ዓመታት ጀምሮ እያከናወነው የመጣው የጎንደር እህትማማችነት ከተሞች (Sister Cities) ግንኙነት ያስገኘው ፋይዳ እጅግ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ይህንኑ ተግባር አስፋፍቶና አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ ይሆናል።

ሐ/ ዲያስፖራዎች ያለባቸውን የጊዜ እና የገንዘብ ችግር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቢያንስ በሚኖሩበት አካባቢ በአክሲዮን እንዲደራጁና እንዲሰሩ በማድረግ በዘለቄታዊነት የልማቱ ተሳታፊ እንዲሆን የማድረግ ስራ መሰራቱ መቀጠልና መጠናከር አለበት።

መ/ ዲያስፖራች ቢገቡባቸው ቅድሚያ ሊሰጥባቸው የሚችሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማሳየት እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን በዚህም በመድሃኒት፣ የህክምና ዕቃዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶችንና ኬሚካሎችን በማምረት እንዲሁም በአግሮ ፕሮሰሲንግ በመሳተፍ የውጭ ምንዛሬ ችግር ሳይገጥም ግብዓቱን ከውጭ እየላኩ እንዲሰሩ እና የቤትና የሆቴል ችግር እንዲቀረፍ ደግሞ በሪልስቴት፣ በሆቴል፣ በሎጅ፣ ሞልና አፓርትመንት እንዲሳተፉ በማድረግ በዘላቂነት የልማቱ ተሳታፊና አስቀጣይ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ መስራት ተገቢ ይሆናል።

## 4.2. በቀጣይ በተለያዩ እርከን ባሉ የመንግስት አካላት ሊደረጉ የሚገባ ጉዳዮች

በዚህ ዘርፍ ከፌደራል መንግስት እስከ ከተማ አስተዳደር ድረስ ያሉ የመንግስት አስፈፃሚና ፈፃሚ አካላት የዲያስፖራውን ተሳትፎ ለማጠናከር በርካታ ተግባራትን ማከናወን አለባቸው፡፡

ከእነዚህም ውስጥ፡-

ሀ/ በፌደራል መንግስት ደረጃ ሊደረጉ የሚገባቸው እንደ አገር ዲያስፖራው ያለውን በጎ ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ከፖሊሲ ማስተካከል ጀምሮ ዲፕሎማቶች ከሚያደርጉት የገፅታ ግንባታን በመመሪያ ደግሞ ዲያስፖራው ባለው አቅም ክፍተት እንዲሞላ በርካታ ማሻሻያዎችን መስራት የመሳተፊያ ኢንተርኮንቲኔንታል ፎረሞችን ማጠናከር፡፡

ለ/ በክልል ደረጃ ክልሉ ያለውን ፀጋ እና አቅም መሰረት በማድረግ ክልላዊ መመሪያ እና አቅጣጫ በመስጠት ልዩ ትኩረት ቢሰጥ፡፡

ሐ/ በከተማ ደረጃ ዲያስፖራው የሚመጣው ከተማውን ለማልማት ስለሆነ ይህን ጉዳይ ልዩ ትኩረት በመስጠት

- አላስፈላጊ ቢሮክራሲን መቀነስ፤
- ያላቸውን የቆይታ ጊዜ አጭር መሆኑን ግንዛቤ በመያዝ ልዩ ስልት ቀይሶ መስራት፤
- የመረጃ ስርዓታችን ማመዘን ለዚህም ከማኑዋል ስራ ተላቆ የሶፍትዌር ስርዓትንና ቴክኖሎጅን በመጠቀም ስራን ማቀላጠፍና ባሉበት ሆነው መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ከፍተኛ አመራሮች በየአገሩ የሚያደርጉትን ቅስቀሳ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ዲያስፖራው ወደ አገር ቤት ሲመጣ በዛ ልክ ማስተናገድ፤
- ዲያስፖራውን እና የውጭ እህት ከተሞች ግንኙነትን ለማጠናከር የተቋቋመውን የትበልፅግ ጎንደር የፕሮጀክት ዩኒት የበለጠ ማጠናከር፤

## ማጠቃለያ

በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በአገሩ የልማት እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረው ተሳትፎ የተጠናከረ እንዲሆን በዋናነት ግንኙነትን ቀጣይና ተከታታይ የማድረግ ስራዎችንም በአደረጃጀት እና በአሰራር በማዘመን የዲያስፖራ ማህበረሰብ ኃይሉን ማስተባበር ከተቻለ የሚኖረው ውጤት እጅግ አመርቂ እንደሚሆን ይጠበቃል። ስለሆነም ከተማችን ጎንደር እንደ መንግስት የሚደረገውን ጥረት አሳታፊ እንዲሆን ለማስቻል የዲያስፖራው አጋርነት ወሳኝ በመሆኑ ከዚህ በፊት በዲያስፖራው የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ጥቅም ላይ በማዋል፣ አዳዲስ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ግፊት በማድረግ የልማት ኃይል የማበራከት ስራ ሲሰራ ቆይቷል። ይህ ተቋማዊ አደረጃት እንዲኖረው ማድረግ ዘላቂነቱን የሚያረጋግጥ በመሆኑ ይህን ተግባር የሚፈጽም ማስተባበሪያ ዩኒት በከተማው ምክር ቤት እንዲቋቋም ተደርጓል። በመሆኑም አበረታች ውጤቶች በመመዝገብ ላይ ናቸው። ነገርግን ይህን ተቋም በሰውኃይል እና በቁሳቁስ እንዲጠናከር ከማድረግ አኳያ ቀሪ ስራዎች ያሉ ቢሆንም አሁን ባለበት በተቋማዊ ይዘት ዲያስፖራውን በማስተባበር በማኑፋክቸሪንግ፣ በአግሪካልቸር፣ በቱሪዝም በተለይም በአገልግሎት ዘርፍ እንዲሰማሩ የተደረገበት አግባብና ውጤቱ አበረታች ነው።

ሌላው እንደ አሰራር ሊቀሰም የሚገባው ትምህርት በዲያስፖራው የነቃ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ የእህትማማች ግንኙነት እናትስስሮች ናቸው። ከ10 ዓመት ስትራቴጅ እቅዳችን በመነሳት የውጭ አገራት ድጋፍ የሚጠየቁ ተግበራትን በመለየት ድጋፉም የትኛው ከተማ ላይ ሊገኝ እንደሚችል በመለየት ላይ የተመሰረተ የእህትማማች ግንኙነት መፍጠር መቻሉ ተገቢ ይሆናል። የማይጣጣሙ ፍላጎቶች ላይ ግንኙነት መመስረት ውጤት እንደማይኖረው ይታወቃል። ይህ ግምት ውስጥ ገብቶ ፍሪያማ ትስስር እንዲኖር ለማስቻል ፍላጎቶችን መሰረት አድገን መስራታችን እንደ ተሞክሮ ሊወሰድ ይገባል። ሌላው ከዚህትይዩ በአብዛኛው የከተማችን ተወላጆች የሚኖሩባቸው ከተሞች ላይ ትኩረት አድርገን መስራታችን መቀጠል አለበት። ይህ የዲያስፖራውን ሃይል አደራጅተን ለመጠቀም የፈጠርነው እድል ከፍ እንዲል በማድረጉ የተሻለ ውጤት እንድናመጣ አግዞናል።

ሆኖም እነዚህ ጠንካራ አፈጻጸሞቻችን እንዳሉ ሆነው በድክመት የሚስተዋሉ ችግሮች አሉብን። ከዚህም ውስጥ አንዱና ዋነኛው የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጠፋና ከውጣ ውረድ የጸዳ ከማድረግ አኳያ አሁንም ድረስ ችግር አለ። በተለይም ዲያስፖራው አቅዶ ወደ አገሩ የሚመጣው ለአጭር ጊዜ መሆኑን ተገንዝበን በእነሱ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ሆነንአገልግሎት ማቅረብ ባለመቻላችን የተስፋ መቁረጥ ስሜት

አድሮባቸው እንዲመለሱ በማድረግ በልማት ስራችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳረፈ መሆኑ ግልፅ ነው። ሌላው ቀለጣፋና ግልጽ አሰራር እንዲኖር ለማስቻል የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት በአግባቡ አለመገንባታችን እና ቴከኖሎጂን መሰረት ያደረግ ስርዓት አለመጠቀማችን ነው። በመጨረሻ እንደ ችግር የሚቀመጠው ዲያስፖራውን በምናሳምንበት ወቅት ቃል የምንገባውን ያህል በተግባር አለመገኘታችን ከአመራሩ የሚስተዋል ችግር ነው። እነዚህን ማነቆዎች መፍታት ከተቻለ በማህበራዊ እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ ልማት የተሻለና ለሌሎች የአገራችን ከተሞች አርአያነት ያለው ውጤት ለማስመዝገብ የምንችገርበት ምክንያት አይኖርም።

## ክፍልሁለት፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ልማት ስራዎች የዲያስፖራ አካላት ተሳትፎ ተሞክሮ ሠነድ (Diaspora Engagement in Development Endeavors of Addis Ababa City)

## ምዕራፍ አንድ፡- አስፈላጊነትና መነሻ ሁኔታዎች

### 1.1. መግቢያ

አዲስ አበባ ከተማ የሀገራችን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የኢንቨስትመንት እና የአፍሪካ የዲፕሎማቲክ ዋና ከተማ ከመሆኗ ባሻገር የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎችና ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚገኙበት ከተማ ነች፡፡

ከዚህ ባሻገር አዲስ አበባ ከ21 ዓለም አቀፍ ከተሞች ጋር የእህትማማችነት ግንኙነት በመፍጠር ከተማዋ በተለያዩ የትብብር መስኮች ተጠቃሚ እንድትሆን እየተሰራ ይገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላትን በከተማዋ በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ተሣታፊ ለማድረግ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከዲያስፖራ ኤጀንሲና ከኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበር ጋር በቅንጅት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በአዲስ አበባ ከተማ በሆቴል ዘርፍ፣ ፔንሲዮን አገልግሎት፣ ዓለም አቀፍ ሬስቶራንት፣ ባህላዊ ሬስቶራንት፣ በማኑፋክቸሪንግና ኢንዱስትሪ በመሣሠሉት ዘርፎች በመሣተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለምሣሌ ያህልም ኩሪፍቱ፣ አዱላላና 2 ሺህ ሀበሻ የባህል ሬስቶራንት የመሣሠሉት የዲያስፖራ አባላት ድርጅቶች ናቸው፡፡ አዲስ አበባ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንደመሆኗ መጠን በከተማዋ የሚገኙ የኢንቨስትመንት አመራጮች በሠነድ መልክ ተዘጋጅቶ እንዲሠራጭ ተደርጓል፡፡

የክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ ጥሪን ተከትሎ በርካታ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መግባታቸው ይታወቃል፡፡ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የዲያስፖራ አባላት በከተማችን የሚካሄዱ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እንዲጎበኙና በከተማችን ያለውን የኢንቨስትመንት አማራጮችን በተመለከተ በአዲስ አበባ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊዎች ማብራሪያ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ዲያስፖራው በሀገሩ ልማት ንቁ ተሣታፊ እንዲሆን የሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በ**"No More"**ዘመቻ የታየው የዲያስፖራ ተሳትፎ እንዲቀጥል ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡
ስለሆነምዲያስፖራው በዕውቀቱ፣ በፋይናንስና በጉልበቱ በሀገር ግንባታ የበኩሉን አስተዋፆኦእንዲያደርግ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጀት መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 1.2. መነሻ ሁኔታዎች/ቀደምሲል የነበሩ ችግሮች

በከንቲባ ጽ/ቤት የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የዲያስፖራ ጉዳዮችን ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ ቢሆንም የተደራጀ የሠው ኃይልና መረጃ አለመኖር፤ የባለድርሻ አካላት ተሣትፎ ማነስና በሌሎች መሠል ችግሮች ምክንያት ዲያስፖራውን በማስተናገድ ረገድ የሚጠበቀውን ያህል እንቅስቃሴ አልተደረገም። ስለሆነም ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር የበለጠ ተቀናጅቶ መስራትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህንን ስራ በተሻለ አደረጃጀት ማሳካት እንዲቻል ከዚህ በፊት የነበረውና የታጠፈውን የዲያስፖራ ማስተባበሪያ ዴስክ መልሶ ማደረጀት አስፈላጊ መሆኑ ባለድርሻ አካላት አበክረው ይገልፃሉ። በሌላ በኩል ዲያስፖራው እሴት በሚጨምሩና ለከተማችን ብሎም ለሃገራችን መለወጥ ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው ዘርፎች እንዲሰማራ ማድረግም የሚጠበቅ ሲሆን የተወሰኑ የዲያስፖራ አባላት አስፈላጊውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ሰነድ ሳያቀርቡ መሬት ለመውሰድ የሚያደርጉት እንቅስቃሴንም እያረሙ መሄድ ይጠይቃል።

## 1.3. የተሞክሮው ዓላማዎች

### 1.3.1 ጥቅል ዓላማ

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት በከተማችን በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች የነቃ ተሣትፎ እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

### 1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት በከተማችን ያለውን የኢንቨስትመንት አማራጮች በማየት ተሣታፊ እንዲሆኑና የተካሄደበት መንገድ ማሳየት፤
- የዲያስፖራ አባላት ለሀገራቸው አምባሳደር መሆን ከተማችንን ብሎም ሀገራችንን የማስተዋወቅ ሥራ እንዲሰሩ የሚደረጉ ጥረቶችን ማሳየት፤
- ዲያስፖራው ለዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ማሳየት፤
- አዲስ አበባ ከተለያዩ ሀገራት ከተሞች ጋር ያላት ትሥሥር እንዲጠናከር ዲያስፖራ የበኩሉን አስተዋፆኦ እንዲያደርግ ማመላከት፤
- በከተማችን በሚካሄደው ሰው ተኮርና ድሃውን ያማከሉ ሥራዎችም ላይ ዲያስፖራው ተሣታፊ እንዲሆን ማድረግ፤
- በከተማችን በሚካሄደው የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችም ዲያስፖራ ተሣታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ለሌሎች ኢትዮጵያውያንን ያለውን ልምድ ማከፈል እንደሚችል ማሳየት፤

- ዲያስፖራው ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል የቦንድ ግዥ ተሣታፊ መሆኑን ማሳየት፤

## 1.4. ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት

- በአዲስ አበባ ከተማ የተገኘውን ተሞክሮ የመቀመር በሌሎች የሀገራችን ከተሞች ለማስፋፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
- የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በአዲስ አበባ ከተማ የሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ያለውን ተሣትፎ በማሳየት ሌሎች ከተሞችም አብነቱን ለመውሰድ ስለሚስያችል፤
- ዲያስፖራውን በተለያዩ የልማት መስኮች ለማሳተፍ በሚደረገው ጥረት የታዩ አበይት ችግሮች በሌሎች ከተሞች መሠል ችግሮች እንዳይደገሙ ለማድረግ ነው፡፡

## 1.5. ተሞክሮውን ለመቀመር የተካሄደበት አግባብ

- በሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዲያስፖራውን በማስተናገድና ድጋፍ በመስጠት ረገድ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት፤
- በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ዲያስፖራ በማስተናገድ ረገድ ያላቸውን ቅንጅት ምን እንደሚመስል በመገምገም፤
- ከኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበር መረጃ በመሰብሰብ፤
- ከዲያስፖራ ኤጀንሲ አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብ፤

## 1.6. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ ትኩረት መስኮች

- በከተማችን ያሉትን የኢንቨስትመንት አማራጮች በወቅቱ የማዘጋጀት፤
- የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር፤

## 1.7 የከተማው ነባራዊ ሁኔታ

### 1.7.1. የከተማዋ አመሰራረትና አወቃቀር ታሪካዊ ምዕራፎች

በሀገራችን በ1999 ዓ.ም በተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ብዛት 3.38 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከ5.2 ሚሊዮን በላይ ህዝብ እንደሚኖርባት ይገመታል፡፡ አዲስ አበባ የሀገሪቱ ዋና ከተማ ብቻ ሳትሆን የኢኮኖሚና የፖለቲካ እንቅስቃሴም ማዕከል ነች፡፡ የከተማዋ አመሰራረት በሚመለከት የተለያዩ መረጃዎች ቢኖሩም በ1879 ዓ.ም በአፄ ሚሊኒክ እንደተቆረቆረች

የ ታ ሪ ክ ሰ ነ ዶ ች ያ መ ል ክ ታ ሉ ፡ ፡ አዲስ አበባ 520 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋትያላት መሆኑን የተለያዩ ሰነዶች ይገልፃሉ።

ከተማዋ ከባህላዊ ከተማነት ወደ ዘመናዊነት ለመሸጋገር የመጀመሪያ እርምጃ የተወሰደው በ1926 ዓ.ም በማዘጋጃ ቤት ደረጃ በአዲስመልክ ስትደራጅ ነው። ይህች ከተማ በጊዜው በንጉሱ በቀጥታ በሚሰየም በአንድ ከንቲባና 16 የሚጠጉ የሥራ ክፍሎች እንዲኖራት ተደርጎ ነበር። በወቅቱም ከተማዋ በ8 አውራጃዎች፣ በ10 ወረዳዎችና በ30 ምክትል ወረዳዎች የተከፋፈለች ነበር።

ከተማዋ ከ20 ዓመታት በኋላ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሷ የሆነቻርተር በሕግ የፀደቀና በዚህም ከተማዋ ርስትና ቤት ያላቸውና በሕዝብ የተመረጡ አባላት ያሉት ምክር ቤት ተመስርቶ ከንቲባው ሁሉንም የከተማዋን አስተዳደር ይዞ ይመራ ነበር። ከዚህ በመነሳትም ከተማዋከበርካታሀገራት ከተሞች ቀድማ ቻርተር ያላት ከተማ ልትሆን በቅታለች።

በዚህ ቻርተር መሠረት ከተማዋ በፊውዳል አገዛዞች ሥር ሳትሆን በቀጥታ ለንጉሡ ተጠሪ ሆና የራሷን የልማት ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ከሀገር ውስጥና ውጭ የፋይናንስ ምንጭ በመበደር እንዲሁም ቦንድ በመሸጥ ገቢዋን ለማሳደግ የሚያስችል ብቸኛ ሥልጣን ነበራት። በሀገራችን በወቅቱ ከነበረው 9 ሚሊዮን (ዘጠኝ ሚሊዮን) የኢትዮጵያ ሀዝብ መካከል 27 በመቶ የሚሆኑት የአዲስአበባ ከተማ ነዋሪዎች ነበሩ።

በወታደራዊ (ደርግ) መንግስት ጊዜ ከተማዋ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ፣የልማት፣ እንዲሁም የመንግስት የርዕዮተ ዓለም ማዕከል ሆና አገልግላለች። ሆኖም ወታደራዊ መንግስትይከተለው በነበረው ርዕዮ ተዓለም ምክንያት የከተማዋ ስልጣን በከፍተኛሁኔታ ተሸርሸሯል። በደርግ ዘመን የከተማዋ አስተዳደር በአራት እርከን የማዕከላዊ መንግስት ተቀጥላ ሆኖ ከማዕከላዊ መንግስት በሚወርድላት ችሮታ ለከተማዋ ነዋሪና ለሕዝቡ የልማትና የዕድገት ፍላጎት ፋይዳ ያልሰጡ እጅግ ውስን የልማት ሥራዎች በስተቀር የተለየ ስልጣን አልነበራትም።

ከ1983 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም የከተማዋን አጠቃላይ አደረጃጀትና አስተዳደር የወሰኑትበሽግግር መንግስት የወጣው ቻርተርና የ1987 ዓ.ም የኢፌዴሪ ሕገመንግስት ናቸው። በተለይ በሽግግር መንግስቱ ወቅት በአዋጅ ቁጥር7/1984 መሠረት ከተማዋ የፌዴራሉን መንግስት ከመሰረቱት ክልሎች

እንዲሆና በአራት አስተዳደር እርከን ትመራ ነበር (በማዕከል፣ በ6 ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት፣ በ28 የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት እና በ328 ቀበሌዎች (305 የከተማ እና 23 የገጠር ቀበሌዎች) ነበሯት። ስለሆነም በ1984ዓ.ም በፌደራል መንግስት ምስረታ ወቅት ከክልሎች ጋር ተመጣጣኝ ስልጣን የነበራት ሲሆን በ1987 ዓ.ም በጸደቀው ህገመንግስት ተከትሎ ለፌደራል መንግስት ተጠሪ በመሆን በቻርተር የተቋቋመች ከተማ ሆናለች።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 49 ራስን በራስ ማስተዳደር እንዲችል የተደነገገ ሲሆን ይሄንንም ለማስፈጸም ከተማዋን ለማስተዳደር የሚያስችል ቻርተር በአዋጅ ቁጥር 361/1995 (እንደተሻሻለ) ታውጇል። የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በ1995 ዓ.ም ከተማዋ የምትመራበትን ቻርተር በማሻሻል የከተማዋ የአስተዳደር እርከን አራት የነበረው ወደ ሦስት አስተዳደር እርከኖች (ማዕከል፣ በ10 ክፍለከተማዎች፣ በ201 ቀበሌዎች ታጥፎ) ዝቅ በማድረግ በመቀጠል በ1996ዓ . ም 201 ቀበሌዎች ወደ 99 ቀበሌዎች እንደገና ተዋቅሯል።

በቻርተሩ የታየው ሌላው ለውጥ የከተማዋን አስተዳደር በሁለት ዋና ዋና ዘርፎች ማለትም የመንግስታዊ አገልግሎትና የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት በሚል የተከፈለበትና የመንግስታዊ አገልግሎቶች በከንቲባ የሚመሩ የቢሮ ኃላፊዎች እንዲሁም የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ደግሞ በዋና ሥራ አስኪያጅ የሚመሩበትን ዓለም አቀፍ ልምድን መነሻ ያደረገ አደረጃጀትን ያስገኘ መሆኑ ነበር።

በ2001 ዓ.ም የመሠረታዊ የሥራሂደት ለውጥ ተከትሎ አዲስ አበባ ከተማበ 10 ክፍለ ከተማና 99ኙ ቀበሌዎች በ116 ወረዳዎች ያደራጀች ሲሆን የወረዳዎች ቁጥር እንዲያድግ ዓይነተኛ ምክንያት የነበረውም በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የቀበሌ አስተዳደሮችን ወደ ወረዳ በመቀየር በተሟላ መልኩ ለነዋሪዎች ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ሰፋፊ የሆኑና ከፍተኛ የህዝብ ብዛትያለባቸውን ቀበሌዎች መለየትና ማካፈል በማስፈለጉ ነበር። ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የአዲስ አበባበ 11ክ/ከተማና በ120 ወረዳዎች የተከፋፈለች ናት።




## 1.7.2. የከተማዋ መሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት

ሰንሰለታማውን የእንጦጦ ተራራን ጨምሮ ከ2120 - 3200 ሜትር ከፍታ ያላት አዲስ አበባ የሙቀት መጠን በአማካይ16 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን አየሯ ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚመጣ ህዝብ የሚስማማ ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ የአፍሪካ ህብረት እና ሌሎች አለም አቀፍ ድርጅቶች ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባ ከመቶ በላይ የተለያዩ ሀገራት ኢምባሲዎችና ቆንስላዎች ጽ/ቤት መገኛም ነች፡፡

## 1.7.3. የከተማው የኢኮኖሚ ምንጭ

በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው የኢኮኖሚ ዘርፍ ስንመለከት የአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚ ሲሆን 74.2 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ 24.4 በመቶና ግብርና 1.3 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ በንዑስ ዘርፍ ስንመለከተው ደግሞ ሰባቱ ማለትም ንግድ ዘርፍ (43.16%)፣ ማኑፋክቸሪንግ (12.66%)፣ ኮንስትራክሽን (10.24%)፣ የገንዘብና መድንተቋማት (13.79%)፣ ትራንስፖርትና መጋዘን (4.94%)፣ መረጃና መገናኛ (2.26%)፣ ምግብና ማረፊያ አገልግሎቶች (1.02%) በድምሩ አማካይ 88.07 በመቶ ድርሻ ሲኖራቸው የተቀሩት ንዑስ ዘርፎች 11.93 በመቶ ድርሻ እንዳላቸው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም

የከተማዋ አጠቃላይ ምርት አማካይ እድገት በ2013 ዓ.ም 10.05 በመቶ ሲሆን የስራ አጥነት ምጣኔ ደግሞ 18.28 በመቶ ነው።

ይህንን ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በ10 ዓመቱ የከተማችን የልማት ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Strategic Pillars) የተቀመጡ ሲሆን በዋናነትም ጥራትያለው የኢኮኖሚ እድገት እና የጋራ ብልፅግና ማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ፣ የቴክኖሎጂ አቅም እና ዲጂታል ኢኮኖሚ መገንባት፣ ዘላቂ የዕድገት እና የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ፣ የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መሪነት ማረጋገጥ፣ የሥርዓታት ለውጥን ማረጋገጥ፣ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎችን መቋቋምና አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፣ የልማት ተጠቃሚነትን እና ማህበራዊ አካታችነትን ማረጋገጥ፣ የፍትህ ተደራሽነት እና ውጤታማ መልካም አስተዳደር መገንባት እና ዘላቂ የሰላም ግንባታ እና ጠንካራ ከባቢያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትብብር ማረጋገጥ ናቸው።

## 1.8. በከተማዋ የዲያስፖራ አካላትን በተለያዩ የልማት ሥራዎች ለማሳተፍ ያሉምቹ ሁኔታዎች እና ፈታኝ ሁኔታዎች

### 1.8.1. ያሉ ምቹ ሁኔታዎች

- ከከተማችን ከንቲባ ጀምሮ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ አመራሮች ዲያስፖራን ተቀብሎ ለማስተናገድ ያላቸው ተነሣሽነትና ቁርጠኝነት፤
- የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት፣ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና የዲያስፖራ ኤጀንሲ በቅንጅት መሥራት መጀመራቸው፤
- የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ዲያስፖራውን ለማስተናገድ ዝግጅት ማድረጋቸው፤
- የአዲስ አበበ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ህንፃ እድሳት መጠናቀቁና እንግዶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ምቹ መሆኑ፤
- አመቺ የኢንቨስትመንት ህግ መኖሩ፤
- አዲስ አበባ ከተማ የተረጋጋ ሠላምና ደህንነት ያላት ከተማ መሆኗ፤
- የፋይናንስ ተቋማት መበራከታቸው፤

### 1.8.2. ፈታኝ ሁኔታዎች

- ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት ለማግኘት ያለው ውጣ ውረድ፤
- የሚመለከታቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ተቀናጅቶ አለመሥራት፤
- የተደራጀ መረጃ አለመኖር፤
- ዲያስፖራው በሀገሩ የመኖሪያ ቤት ለማስገንባት መሬት የማግኘት ችግር፤

# ምዕራፍ ሁለት፡- የዝግጅት ምዕራፍ

## 2.1. የዲያስፖራ አካላትን በተለያዩ የልማት ሥራዎች የማሳተፍ ዓላማ

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በሀገሩ ልማትና ዕድገት የበኩሉን አስተዋፆኦ እንዲያደርግ ሁኔታዎች ማመቻቸት ሲሆን በዕውቀቱ፣ በፋይናንስ አቅምና በጉልበቱ ተሣታፊ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡አዲስ ዲያስፖራ ማዕከል

ከተከፈተበት ከታህሳስ 20/2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 15/2014 ዓ.ም ድረስ ከ1,500 በላይ የተመዘገቡ እንዲሁም ምዝገባ ያላከናወኑ ዳያስፖራዎች በአካል ተገኝተው በማዕከሉ የተለያዩ መረጃዎችን አግኝተዋል።

## 2.2. የዲያስፖራ አካላትን በዘላቂ የልማት ሥራዎች ለማሳተፍ ያለ ዝግጅት

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲያስፖራ አባላትን በከተማዋ በሚካሄዱ ዘላቂ የልማት ሥራዎች ማሳተፍ ይቻል ዘንድ የሚመለከታቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶችን የማስተባበር ሥራዎች ተሠርቷል።
- ዲያስፖራው ለዘላቂ ልማት ሥራዎች የበኩሉን አስተዋፆኦ ማድረግ እንደሚችል ልዩ ልዩ የውይይት መድረኮች ተዘጋጅቷል።
- የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በኢንቨስትመንት መስክ፣ ቱሪዝም ማሰፋፋት፣ በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ከፍተኛ አስተዋፆኦ ማድረግ የሚችል መሆኑን ግንዛቤ እንዲፈጠር ጥረት ተደርጓል።
- የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ከተማችንን በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ ድርሻ መጫወት እንደሚችል ግንዛቤ ተፈጥሯል።

### 2.2.1. በየደረጃው ያሉ አስተዳደሮች ግንዛቤ በመፍጠር ዳያስፖራ ተኮር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች (ቀጥታ ኢንቨስትመንት፣ ስራ ዕድል፣ ሬሚታንስ፣ ዲያስፖራ ቦንድ) ላይ ከማሳተፍ አኳያ

- የዲያስፖራው አባላት አብዛኛው ማለት በሚያስችል መልኩ በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ መሳተፍ የሚፈልግና ከነበረበት ሀገርም አማራጭ የስራ ዘርፎች ይዞ በመምጣት ለመሰማራት የነበረው ተነሳሽነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።
- በዚህም በተለይም በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል። በየትኛው ስራ ዘርፍ ላይ መሳተፍ እንዳለባቸውና ትኩረት የሚደረግባቸው ዘርፎች የትኞቹ ናቸው የሚለውንም ለማስገንዘብ ተሞክሯል።
- በተጨማሪም በአዲስ አበባ የኢንቨስትመንት ኮሚሽንና የፌደራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በጋራ በመሆን በስካይ ላይት ሆቴል ለ4 ቀናት የኢንቨስትመንት ፎረም በማዘጋጀት ከ1,500 በላይ የዳያስፖራ አባላት ተገኝተው በቂ የሆነ ግንዛቤና ማብራሪያ የተሰጠበትና በመንግስትም ያለው ዝግጁነትና ተነሳሽነትን አሳይቷል።

- የምገባ መርሃ ግብሩ ስራ በከተማ አስተዳደሩ እየተሰሩ ያሉትን ስራዎች ከቅድመ አንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የሚደረገውን ድጋፍ የግብዓት አቅርቦት እንዲረዱት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ዕለት ጉርስ የሌላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በቀን አንድ ጊዜ የሚከናወነውን ምገባ እንዲያግዙና እንዲደግፉ ለማድረግ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ በራሪ ወረቀቶችን በመስጠት እንዲሁም በተጨባጭም በተስፋ ምገባ ማዕከላት በመገኘት እንዲጎበኙ በማድረግ የምገባ ፕሮግራሙን እንዲረዱትና እንዲደግፉት ለማድረግ ተሰርቷል፡፡ በዚህም 7ተኛው የተስፋ ምገባ ማዕከልን የዲያስፖራው ማህበረሰብ ለመገንባት ከምገባ ኤጀንሲ ጋር ውይይት አካሂደዋል፡፡
- በታላቁ የህዳሴ ግድብ ተሳትፎ ረገድም ቢሆን በአካል ሄደው ማየት ባይችሉም ያላቸውን ተሳትፎ በንድ በመግዛትም ጭምር አረጋግጠዋል፡፡ በዚህም **536,718.77 (አምስት መቶሰላሳ ስድስት ሺ ሰባት መቶ አስራ ስምንት ብር)** የሚያወጣ በንድ በአዲስ የዲያስፖራ ማዕከል ብቻ ግዥ ፈጽመዋል፡፡
- በማዕከሉ በነበረው መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ 130 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደዋል፡፡ በከፊል በዝርዝር ለማሳየት 43 በማምረቻ ፣18 ህንፃ ግንባታ ቅይጥ አገልግሎት፣ 9 የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ማከራየት፣4 ባለ ኮከብ ሆቴል፣ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ 5 መካከለኛ ክሊኒክና የህክምና ማዕከል፣ 4 በትምህርት ዘርፍ፣ 3 ቱርና ትራቭል፣ 3 መረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሌሎችም የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተዋል፡፡ ከ130 ውስጥ 1በመረጃ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ያወጡ ወደ ስራ ላይ ገብተዋል፡፡




## 2.2.2. የዕውቀትና የክህሎት ሽግግር ከማድረግ አኳያ

- የዲያስፖራው አባላት ሀገር ከመጎብኘት ባሻገር ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ ሊያሰፋ በሚያስችል መልኩ ሙያዊ በመሆኑ ሁኔታ ለመደገፍና ለማገዝ ሞክረዋል፡፡ **ለምሳሌ፡**- በህክምና ዘርፍ ላይ ግንባር ድረስ ሄደው ህክምና የሰጡና ለመስጠትም ፍቃደኛ የነበሩ፤ በጎዳና ተዳዳሪዎች ላይ የምክር አገልግሎት ለመስጠት፤ የበጎ ፈቃደኝነት ስራ ለመስራት ዝግጁ የሆኑ የዳያስፖራ አካላቶች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡
- በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት በአዲስ አበባ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ድጋፍ ከዳያስፖራው አባላት ተገኝቷል፡፡
- በአሜሪካ (አትላንታ) ኑሯቸውን ያደረጉና የጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ ጥሪን ተቀብለው አገር ቤት የገቡ ዳያስፖራዎች ያቋቋሙት **የትስ ፋሚሊ ፋውዴሽን** ወጣት የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ ከአዲስ አበባ ከተማ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮጋር የስምምነት ሰነድተፈራርመዋል፡፡
- ፕሮጀክቱ በሙከራ ደረጃ ለ15 ሴት ሰልጣኞች ድጋፍ በማድረግ የጀመረ ሲሆን ሰልጣኞች ከስልጠናም በኋላ የራሳቸውን ስራ ፈጥረው ወደ ስራ እንዲገቡ ድጋፍ የሚደረግላቸው ይሆናልም ተብሏል፡፡ በቀጣይ ሌሎች በርካታ ወጣት ሰልጣኞችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡




## 2.2.3. ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም ሀብት በማሰባሰብ ረገድ ያላቸው ተሳትፎ፤

